# የሕዝብ ድርጅትና የፖለቲካ ት/ቤት ሚና በኢትዮጵያ አብዮት ውስጥ

ዋጋው 0.25 ሳንቲም

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

# የሕዝብ ድርጅትና የፖለቲካ ትምህርት ቤት ሚና በኢትዮጵያ አብዮት ውስጥ

በአራተኛው ዓመት የአብዮት በዓል
የማስታወቂያና የፕሮፓጋንዳ ኮሚቴ
የ ተ ዘ ጋ ጀ

መስከረም ፲፱፻፸፩—አዲስ አበባ ።

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

# ማውጫ

**<u>ይዘት</u>** **<u>ገጽ</u>**


— መቅድም . . . . . . . . . . . . . ፫

— የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት . . . . . . . . . . . . ፯

— የየካቲት ፳፮ ትምህርት ቤት በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ውስጥ የተጫወተው ሚና . . . . . . . . . ፲፱

# መ ቅ ድ ም

የኢትዮጵያ አብዮት ከወለዳቸው ታላላቅ ተቋሞች መካከል የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤትና የየካቲት ‘፷፮ የፖለቲካ ትምህርት ቤት ሳይወሱ የሚታለፉ አይደሉም ። ምክንያቱም የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤትና የየካቲት ‘፷፮ የፖለቲካ ትምህርት ቤት በኢትዮጵያ አብዮት ውስጥ እስከዛሬ የተጫወቱት ሚና እጅግ ታሪካዊ ነው ። በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ውስጥ በተለይ የብሔራዊው ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም እንዲታወጅ የተፈጠሩት እነዚህ ከፍተኛ ተቋሞች ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በማርክሲዝም-ሌኒንዝም ርዕዮተ-ዓለም ለማነጽ በሰፊው ለማስተማር በተደረገውና በሚደረገውም ትግል ውስጥ እጅግ ጉልሕ የሆነ አስተዋጽኦ አበርክተዋል ። እያበረከቱም ናቸው ። በተለይ ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በማንቃት በማደራጀትና ለትጥቅም እንዲበቃ በማድረግ አንፃር እነዚህ ሁለት ድርጅቶች ከፍ ያለ ትግል አድርገዋል ። በዚህም ትግላቸው ወቅት አያሌ ታጋይ ጓዶቻቸው በፀረ —



INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

አብዮተኞች ሤራ ወድቀዋል ። አድኃርያን በነዚህ ድርጅቶች ላይ እጅግ ከፍ ያለ ዘመቻ ያካሄዱባቸው ቢሆንም እነዚህ በትግል የተገኙ ድርጅቶች የሰፊው ሕዝብ አብዮት ደረጃ በደረጃ እየተጠና ከረና በድል ላይ ድልን እየተቀዳጀ እንዲሄድ ከፍ ያለ ሚና ተጫውተዋል ።

ለመሆኑ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ እነዚህ ድርጅቶች በዝርዝር ያከናወኗቸው ምንድን ናቸው ? ወደፊትስ የእነዚህ ድርጅቶች ግብ ምንድን ነው ? ለእነዚህና እነዚህን ለመሰሉት ጥያቄዎች ምላሽ በሁለት ክፍል በቀረበው በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ባጭሩ ተገልጿል ።



# የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት

በአዲሱ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ማዕበል ውስጥ የሚገኘው የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ እንቅስቃሴውን በግብታዊ መልክ ጀመረ ።

በፊውዶ-ቡርዧ አስከፊ የብዝበዛ ሥርዓት ውስጥ ለዘመናት ሲማቅቅ የነበረው ጭቁኑ የቀድሞውን አገዛዝ በእምቢተኛነት ለመቃወም ነባራዊው ሁኔታ ሲፈቅድለትና ሲያስገድደው በወቅቱ ሊሟላ ያልቻለው ሕሊናዊው ሁኔታ የተቀነባበረ የፖለቲካ አመራርን አለማግኘቱ ነበር ። ይህም በመሆኑ ነበር በወቅቱ በአንፃራዊ ትጥቅና ድርጅት ላቅ ያለው ክፍል ማለትም የመለዮ-ለባሹ ክፍል የአመራሩን ሥልጣን ለመያዝ የበቃው ።

ይኸው የአመራር ለውጥ ከተከሠተም በኋ በግንፍልነት የተነሣው የሰፊው ሕዝብ እንቅስቃሴ መሠረታዊ ለውጦችን በማስከተል ፤ ከጊዜ ወደጊዜ እየዳበረ እያደገና ፈርም እየያዘ መጣ ።

የአመራሩንም ሥልጣን የያዘው ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚ

ካሂደውን የመደብ ትግል በውስጡም እያንጸባረቀ ለአብዮቱ ዕድገት መሳካትና መስተካከል አመቺ ሁኔታን መፍጠር ዋነኛው ተግባሩ አደረገ ። ቀደም ብለው በአዋጁ የተበሠሩትን የሕዝብ ድሎች ማለትም ፤—

—የዘውድ አገዛዝ መገርሰስ ፤

—የማምረቻና የማከፋፈያ ድርጅቶች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር መዋል ፤

—የእድገት በኅብረት ፤ የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ

—የገጠር መሬት የሕዝብ መሆን ፤

—የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር መዋል . . . . ወዘተ

የሰፊውን ሕዝብ ይበልጥ መንቃት ፤ መደራጀት ለትጥቅም መብቃትና ያገኙትን ድል ለመከላከል መቻል ከመቼውም ይበልጥ አጉልቶ አመጣው ። ይህ ሁሉ ሲሆን አሁንም የፖለቲካ አመራሩን አቀነባብሮ ሊሰጥ የሚችል የፖለቲካ ድርጅት ገና አልተከሠተም ።

በዚህን ታሪካዊ ወቅት ነበር ፤ ቀደም ሲል ተወስደው የነበሩትን ተራማጅና ሥር-ነቀል እርምጃዎች በማስፈጸም ረገድ በትግል መስኩ ውስጥ ይሳተፉ የነበሩ ግለሰቦችን በአንድ ሕጋዊ የጋራ



INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

መድረክ ሰብስቦ የተቀነባበረ የፖለቲካ አመራር ማስገኘት ያስፈለገው ።

ይኸው ሕጋዊ የጋራ የትግል መድረክ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ ቤት ነበር ።

ለዚህ ከታጩት ከ፶ የሚበልጡ ግለሰቦች ፲፰ ፈቃደኛ ሆነው ብቁነታቸውም ታምኖበት የጉባኤ አባል ሆነው ሲመረጡ ፤ በዚያን ወቅትም የትሮትስካይቱ የኢ.ሕ.አ.ፓ. ቡድን ይህንን አዲስ ተቋም ተጻርሮት ነበር ።

፲፰ቱ የጉባኤ አባላት በጥር ፲፱፻፷፰ ሥራቸውን ጀምረው በሚያዝያ ፲፱፻፷፰ የጽ/ ቤቱና በወቅቱም በሥሩ የነበረው የየካቲት ፷፮ የፖለቲካ ት/ ቤት መመሥረት በአዋጅ ተበሠረ ። እብሮም የአብዮታችን መመሪያ «የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም» ተበሠረ ። በ፲፱፻፷፰ ከወጣው አዋጅ የጽ/ ቤቱን ሥልጣንና ተግባር ዋና ዋናዎቹን ከዚህ ቀጥለን እንጠቅሳለን ።

—«የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን መከታተል ፤

—የኅብረተሰብአዊነት ፍልስፍና እንዲስፋፋ የሚረዱ ጽሑፎችንና መመሪያዎችን በልዩ

ልዩ ብሔረሰቦች ቋንቋዎች አዘጋጅቶ በልዩ ልዩ የመገናኛ ዘዴዎች በየክፍለ ሀገሩ ፤ በየአውራጃው ፤ በየወረዳውና በየቀበሌው እንዲደርሱ ማድረግ ፤

—የሰፊውን ሕዝብ የበላይ ገዢነት የሚያረጋግጥ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሬፑብሊክ የሚቋቋምበት አመቺ ሁኔታ እንዲፈጠር ማገዝ ፤

—በዚህ መሸጋገሪያ ጊዜ ለሥራ ቅልጥፍና እንዲያመችና ለአብዮታዊ እርምጃዎች መሰናክል እንዳይሆን ያለው የቢሮክራሲ አቋም በሰፊው ሕዝብ ትግል የሚለወጥበትን መንገድ መጠቆም ፤

—የሰፊውን ሕዝብ የመደራጀት ጥረት ለማገዝ የፖለቲካ አንቂዎች በውጪና በሀገር ውስጥ የሚሠለጥኑበትን መመሪያ ፤ እቅድና ፕሮግራም ማዘጋጀት ፤

—በመሸጋገሪያ ጊዜ የሚፈጠሩ የኤኮኖሚና የሶሺያል ችግሮች የሚቃለሉበትን ዘዴ ማጥናት … » የሚሉት ይገኙበታል ።

ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎችንም ተግባሮቹን ለመወጣትና በዋናው ጉባኤ ደረጃ ሥራውን በአራት ኮሚቴዎች ከፋፈለ ፤ እነሱም ፡—



ሀ/ የፍልስፍና ማስፋፊያና የማስታወቂያ ኮሚቴ ፤

ለ/ የፖለቲካ ትምህርት ኮሚቴ ፤

ሐ/ የጊዜያዊ ጉዳዮች ኮሚቴ ፤

መ/ የድርጅት ጉዳይ ኮሚቴ ናቸው ።

በየክፍለ ሀገሩ በየአውራጃውና በየወረዳው ቅርንጫፍ ጽ/ ቤቶች በመክፈት በየደረጃው ለየቦታው የሚመጥኑ ካድሬዎችን ወደሰፊው ሕዝብ አሠማራ ። ይሁን እንጂ አድኃሪዎች ተገንጣይ ቡድኖች በፈጠሩት አስቸጋሪ ሁኔታ እስከ ፲፱፻፷፱ መገባደጃ ድረስ ከጋሞና ሴቲት አውራጃ ዋና ከተማ ባሬንቱ በስተቀር በኤርትራ ክፍለ ሀገር የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ ቤት ቅርንጫፎች አልነበሩም ።

የሰፊውን ሕዝብ ንቃተ ሕሊና ከፍ በማድረግና ማርክሲዝም-ሌኒንዝም እንዲሰራጭ ፤ በመንግሥት ዜና ማሰራጫ (ጋዜጣ ፤ ሬዲዮ ቴሌቪዥን) በመጠቀም በየሁለት ሳምንቱ የምትታተም አብዮታዊት ኢትዮጵያ ጋዜጣን በማዘጋጀት ፤

በየወቅቱ የሚወጣ የቲዎሪ ብሮሹሮችን ( መጽሔቶ ችን ) በማዘጋጀት ይሠራል ።

በተፈጠረው አመች ሁኔታ በመጠቀም ተራ ማጅ ኃይሎች የሰፊውን ሕዝብ ንቃት ከፍ በማድ ረግ ድርጅቶች እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ ታግለ ዋል ።

ለተቀነባበረ ሕዝባዊ ትግል አብዮታዊ ንቃ ትና ድርጅት ማስፈለጉ የታመነበት ሳይንሳዊ ሐቅ ነው ። ይህንን ለማሟላት የወዝአደሩ ፓርቲ ገና ሕልውና ባላገኘበት የኢትዮጵያ አብዮት ውስጥ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ ቤት ሚና በቀላሉ የሚታይ አይደለም ። ፀረ-አብዮት ኃይ ሎች ይህንኑ በመገንዘባቸውና ገና ተግባሩን ከጀ መረበት ጊዜ አንሥቶ አተኩረውበታል ። ሰፊው ሕዝብ ከነቃና ከተደራጀ አንቅሮ እንደሚተፋቸው ቀድሞውኑ ስለተገነዘቡ ይህ ከመሆኑ በፊት ጽ/ ቤቱን እንዳይሠራ ለማድረግ ሸንጣቸውን ገት ረው ተዋግተዋል ። በርካታ የጽሕፈት ቤቱን ካድ ሬዎች ከእነርሱም ጋር አንድነት ያላቸውን ታጋ ዮችና የንቃት ውጤት የሆኑትን የብዙኃኑን ድር ጅት መሪዎች ያለአንዳች ርኅራኄ ረሽነዋል። በተለይ ከ፲፱፻፷፱ መጀመሪያ እስከ ፲፱፻፸ አጋ





ከሰፊው ሕዝብ የተውጣጡ ወዝ-አደሮች ፣ ገበሬዎች ፣ መለዮ-ለባሾች .... በካድሬነት እየሠለጠኑ ተመርቀዋል ።

ማሽ ድረስ የረገፉት ታጋዮች ብዛት በቀላሉ የሚገመት አይደለም ። ጽ/ ቤቱ ምንም እንኳን በርካታ ካድሬዎች ቢሰውበትም የሰፊው ሕዝብ ድጋፍ ስለነበረው ተልእኮውን ማስፈጸሙን ገፋበት እንጂ አላገኮበደደም ። የጨበጠውም የማርክሲዝም ሌኒንዝም ሳይንስ እውነት በመሆኑ እንደየሁኔታው በዚያ እየተመራ ግስጋሴውን ቀጠለ እንጂ አልተፍረከረከም ።

የአብዮታችን መዳበርና መጠናከር በአስከተለው የተለዋወጠ የውስጥና የውጪ ሁኔታ ፤ በጽ/ ቤቱ አማካይነት ይከናወን የነበረውን የፖለቲካ ሥራ ይበልጥ ለማቀነባበርና በተለይም በስውር ይታገሉ ለነበሩ ማሌ ድርጅቶች የወዝአደሩን ፓርቲ ለመፍጠር ይበልጥ አመች ሁኔታ ለማስገኘት የጽ ቤቱ አሠራር መሻሻል አስፈለገ ። ስለሆነም ሐምሌ ፯ ቀን ፲፱፻፷፱ የጽ/ ቤቱን አሠራር በአዲስ መልክ ያሻሻለው አዋጅ ወጣ ። በዚሁ አዋጅ መግቢያ ላይ እንደተጠቀሰው ፤

«...አሁን ያለው የዚህ ጽሕፈት ቤት አቋም ከተሻሻለው የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ አቋም ጋር እንዲስማማ ማድረግ ስላስፈለገና በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ

INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA



አብዮታችን ፕሮግራም መሠረት የወዝአደሩ ፓርቲ እንዲቋቋም ለሚጣጣሩ አብዮታዊ ቡድኖችን ግለሰቦችን ፤ በመንግሥት በኩል የማያቋርጥ ድጋፍ መስጠት አብዮታዊ ግዴታው ስለሆነ በዚህ መሠረት የተደራጁትንና ወደፊትም የሚደራጁትን ተራማጅ ኃይሎች በእኩልነት እንዲያገለግል ማድረግ የተራማጆችን ኅብረት ለማፋጠን የሚረዳ መሆኑ ስለታመነበት . . . » ይላል።

ሥልጣንና ተግባሩ እንደበፊቱ ሁኖ አሠራሩ ግን የተራማጆችን ኅብረት ለማጠናከር እንዲያመች የአሠራሩን ዘዴ በአዲሱ አዋጅ መንፈስ ቀየሰ ። በመሆኑም በዋናው ጽ/ ቤት ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ የጉባኤ አባሎች ቍጥር ከ15 ወደ 5 ተቀነሰ ። በየክፍላተ ሀገሩም አመራሩ በዋናው ጽ/ ቤት ያለውን ጉባኤ በሚያንጸባርቅ መልክ እንዲሆን ተደረገ ። ይኸው የተደረሰበት የትግል ደረጃ መ. ኢ. ሶ. ን. የተባለውን ድርጅት (በውስጡ ቀደም ሲል ጀምሮ ከነበረበት ውጥረት ሌላ) ተጨማሪ የመደናበሪያ ነጥብ ስለሆነበትና ስለአስደነገጠው ካድሬዎቹን ከትክክለኛ የትግል መድረክ አሸሸ ። ማለትም መ. ኢ. ሶ. ን. ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብና አብዮቱን ከቶ ከፀረ አብዮትና ፀረ ሕዝብ ኃይሎች ጋር ተደባለቀ ። ሆኖም ከሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብና ከአብዮቱ ጋር በቆራጥነት በቆሙት ሐቀኛ ታጋዮች

ተጋድሎ የጽሕፈት ቤቱ ተግባር የበለጠ ተጠናክሮ
እንዲቀጥል ለማድረግ ተችሏል ።

ኅብረትን ፈጥረው የወዝ አደሩን ፓርቲ ለመ
መሥረት በኅቡዕ ለመታገል የጽኑ ማርክሲስት-
ሌኒንስት ድርጅቶች በዚሁ ሕጋዊ መድረክ በመ
ጠቀም የኅብረቱን መንፈስና አሠራር ተቀዳሚ
በማድረግ እንደ አንደኛው የትግል መድረካቸው
በመጠቀም በኢ. ማ. ሌ. ድ. ኅ. መጠናከርና ለው
ኅደቱም ሂደት አመቺ ሆኗል ። ይህም በመሆኑ
ቀደም ብለው ለተመሠረቱት የብዙኃን ድርጅቶች
ማለትም ፦

—መ. ኢ. ሠ. ማ.
—መ. ኢ. ገ. ማ.
—ከ. ነ. ማ.

ከውስጣቸው ከፀረ-አብዮተኞች እንዲጸዱ ፤
የተጠናከረ አመራር እንዲያገኙ የተደረገው ጥረ
ትና ትግል እስካሁን ጥሩ ውጤትን ያስገኘ ቢሆ
ንም አሁንም ገና ብዙ ሥራ ይጠበቃል። ለአብዮታችን
ጠንካራ መሠረት ሊሆኑ የሚችሉትንም የሴቶችና
የወጣቶች አገር-አቀፍ ድርጅት ለማቋቋም ከፍ
ተኛ ጥረት በመደረግ ላይ ነው ።

ለአብዮታችን መፈንዳት የነባራዊና ሕሊ
ናዊ ሁኔታዎች በስሎ መገኘት አስፈላጊ ነው።
በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ አብዮት በየካቲት ፲፱፻፷፮



ሲፈነዳ የመጀመሪያዎቹ ሁኔታዎች ተሟል
ተው ሲገኙ ፤ የኋለኞቹ ግን ገና ነበሩ ። በዚያም
የተነሣ የአብዮቱ ፍንዳታ ግብታዊ ከመሆኑም
በላይ ፤ ሂደቱ በአስተማማኝ የመቀጠሉ ጉዳይ
እጅግ አሳሳቢ ነበር ። በተለይም የሰፌው ሕዝብ
የመደብ ጠላቶች ትጥቃቸውን አጥብቀው በተነሣ
ሣቡት ወቅት ሁሉ ፤ የሁኔታው አሳሳቢነት ጎልቶ
ታይቷል ። ይሁን እንጂ በሐቀኛ አብዮተኞችና
በሰፊው ሕዝብ መረባረብ በየደረጃው ከተከሠ
ቱት ቀውጢ ወቅቶች በድል አድራጊነት ለመወ
ጣት ተችሏል ። በዚህ መልክ ብዙ ብንጓዝም ፤
ያ አብዮቱ በፈነዳበት ወቅት ያልተሟላው አስተ
ማማኝ አሠራር ዛሬም የለም ። ዛሬም የወዝአደሩ
ፓርቲ ሕልውና አላገኘም ።

በዚህ መልክ ደግሞ ለዘላቂው ድል መገኘትና
ብዙ ወደፊት መግፋት ይቻላል ማለት ዘበት ነው።
ወዝአደራዊ አመራርን ያልተቀዳጀ ሕዝባዊ ትግል
ከቶውንም አስተማማኝ ሊሆን አይችልም ። የግድ
ይህንን ማሟላት ይኖርበታል። የኢ. ማ. ሌ. ድ. ኅ.
ወደ ከፍተኛ ደረጃ መሸጋገር በዚህ ረገድ ከፍተኛ
ግምት የሚሰጠው ነው ።

አብዮቱ ተጠብቆ በአስተማማኝ ወደፊት ይገ
ሰግስ ዘንድ የወዝ አደሩ ፓርቲ ሕልውና አማራጭ



INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

የሌለው ቢሆንም ፤ የሰፊው ሕዝብ በየፈርጁ መደራጀትም የማይታለፍ ጉዳይ ነው ። የሠራተኞች ማኅበራትን ፤ የገበሬ ማኅበራትን ፤ የከተማ ነዋሪዎች ማኅበራትን ይበልጥ ማጥራትና ማጠናከርና በሚገባ ያልተቋቋሙትንም የወጣትና የሴት ማኅበራት በአገር-አቀፍ ደረጃም ማቋቋምና ማጠናከር እጅግ አስፈላጊ መሆኑ የታወቀ ነው ። በዚህ ሁሉ የትግል መስክና እንቅስቃሴ አንጻር የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ ቤት ዛሬም ከፍተኛ የትግል ድርሻ እንዳለው እሙን ነው ። ስለሆነም ከትግሉ ምጥቀት አኳያ ብቃቱን እያረጋገ የትግል አስተዋጽኦ ማድረግ አሁንም ይጠበቅበታል ።

* * *



# የየካቲት ፷፮ የፖለቲካ ትምህርት ቤት በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ውስጥ የተጫወተው ሚና

ለዘመናት በኢትዮጵያ ተንሰራፍቶ የነበረው የፊውዳሉ ሥርዓት ፤ በ፲፱ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ በ፳ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ አካባቢ የኢምፔሪያሊዝም ወደ ኢትዮጵያ መግባት ያስከተለው ካፒታሊስታዊ ስልተ-ምርት የጭቁን ሕዝቦች ኑሮ ከጊዜ ወደጊዜ እያቆለቆለ እንዲሄድ አድርጓል ። ስለሆነም በበዝባዥና በተበዝባዥ መደቦች መሐል የነበረው ቅራኔ በዚያው መጠን እየከረረ ሄዷል ። ይህም በተበታተነ መልክም ቢሆን አልፎ አልፎ በተደረጉት ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች ሲከሠት ቆይቷል ። ይሁን እንጂ ከተጨባጭና ኅሊናዊ ሁኔታዎች አለመሟላትና ከትክክለኛ አመራር ጉድለት የተነሣ እኒያ ብልጭ ድርግም ሲሉ የነበሩት ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች ቅራኔዎቹን ሊያስወግዱ አልቻሉም ። በመጨረሻ ግን በአገሪቱ የኢኮኖሚ ፤ የፖለቲካና የሶሻል መስኮች በተከሠቱት ሁኔታዎች ለኋሽነትና አራጋቢ



INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

ነት የነዚያ ለዘመናት የታመቁ ቅራኔዎች መፈን
ዳት የየካቲት ፷፮ን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ወለዱ ።

ይህ ፀረ—ፊውዳልና ፀረ—ኢምፔሪያሊስት ይዘት ኖሮት በመላ ኢትዮጵያ ዳር እስከዳር ያስተጋባው እንቅስቃሴ ዛሬም በሚገባ ያልሻረና ያልጠገገ ትልቅ ቁስል ነበረበት ። ይኸውም የሆነው የወዝአደሩ ፓርቲ አመራር ባለመኖሩ ነው ። ስለዚህም ግብታዊ ነበር ። እንደዚያም ሆኖ የኢትዮጵያ አብዮት ድልን በድል ላይ እየተቀዳጀ መጥቶ ዛሬም ካለበት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሊደርስ የቻለው የየካቲቱ ግብታዊ እንቅስቃሴ የተቀጣጠለው አብዮታዊ ሁኔታ ተፈጥሮ በነበረበት ወቅት ስለነበረ ፤ እንደማንኛውም ግብታዊ እንቅስቃሴ በአጭር ስላልተቀጨ ነው ለማለት ይቻላል ። ለእንቅስቃሴው ልዩ ባሕርይ ከሰጡት ምክንያቶች አንደኛው የኢትዮጵያ ተራማጆች በቅድመ-የካቲት የኢትዮጵያ ሰፊው ሕዝብ በፊውዳሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም ላይ ክንዱን እንዲያነሣ ሁኔታው በፈቀደላቸው ጊዜ ሁሉ ሲቀሰቅሱና የፊውዶ-ቡርዧውን ሥርዓት ሲያጋልጡ መቆየታቸው ነው ። ከየካቲት *፷፮ በኋላም የተበታተነውን እንቅስቃሴ

*(አጠቃላይ የኢኮኖሚ ቀውስና የኑሮ መወደድ ፤ በገጠርው መደብ ዘርፎች መሐል ቅራኔ መፈጠር ፤ የወሎ ረሀብ . . . ወዘተ )



ለመሰብሰብና ለመሠረታዊ ለውጥ መንደርደሪያ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል ። ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፊውዶ—ቡርዧው ሥርዓት ብዝበዛና ጭቆና ለአንዴም ፤ ለሁልጊዜም እንዲላቀቅ ለመሠረታዊ ለውጥ ማካሔድ ላለበት አብዮታዊ እንቅስቃሴ የአብዮታዊ ቲዎሪ አስፈላጊነት የሚያጠያይቅ አይደለም ። ዳሩ ግን ፀረ-ዲሞክራቲክ የሆነው የኃይለ ሥላሴ አገዛዝ የተራማጅ አስተሳሰቦችንና የአብዮታዊ ርዕዮተ ዓለምን መስፋፋት በከፍተኛ ደረጃ ይከላከል ስለነበር የወዝአደሩ ርዕዮተ ዓለም ከሆነው ከማርክሲዝም ሌኒንዝም ለመተዋወቅ የቻለው የኅብረተሰብ ክፍል ተማሪው ብቻ ሲሆን ፤ ይኸውም ቢሆን የተወሰነው ቁጥራቸው እጅግ በጣም ጥቂት በሆኑ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አካባቢ ነበር ። ከዚያ በኋላ እያደር በመስፋት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን ተቀባይነት አስከተለ ። የየካቲቱ እንቅስቃሴ መፈንዳት ደግሞ በተከተሉት ጊዜያት ማርክሲዝምን በመጠኑም ቢሆን ለማስፋፋት አመቺ ሁኔታን ስለ



INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

ፈጠረ ወደሀገር ውስጥ የሚገቡ የማርክሲዝም ሥነ ጽሑፎች በረከቱ ።

ከየካቲቱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በኋላ ፤ ከተገኙት በርካታ ድሎች መሐል በኢትዮጵያ አብዮት ታሪክ ውስጥ ትልቅ ሥፍራ የሚይዘው የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መውጣት ለአብዮቱ ርዕዮተ-ዓለማዊ መሠረት ለመጣል የሚያስችል አዲስ ምዕራፍ ከፈተ ። በጭቁኑ ሕዝብ ውስጥ የወዝአደሩ ርዕዮተ ዓለም መስፋፋት ግዴታ መሆኑን በመግለጽ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤትንና የፖለቲካ ትምህርት ቤት የመሰሉ ተቋሞች እንዲቋቋሙ ተደረገ ።

ከብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መውጣት ጋር እነዚህ ሁለት ተቋሞች የተመሠረቱበትን ዓላማ በአጭሩ ለማስቀመጥ ፡—

፩. —የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ግብ መምታት የሚረጋገጠው ወዝአደራዊ አመራር ሲገኝ ብቻ በመሆኑ ፤ አብዮቱን የሚንከባከበው ሰፊ ሕዝብ በጠላቶቹ ፊት ይበልጥ እንዲነቃ ፤ እንዲደራጅና



ለትጥቅ እንዲበቃ አድርጎ የወዝ አደሩ ፓርቲ ሲፈጠር ከሰፊው ሕዝብ ጋር የሚያገናኙት የሕዝባዊ ድርጅቶች እንዲጠናከሩ ለማድረግ ፤

፪. ለአብዮቱ ግብ መምታትና ዘላቂነት በሳይንሳዊ ርዕዮተ-ዓለም የታጠቀ የሰፊው ሕዝብ የነቃ ክፍል ስፋት እንዲጨምር ለማድረግ ነበር ።

በዚህም መሠረት ከግንቦት ወር ፲፱፻፷፯ ጀምሮ የተከፈተው የየካቲት ፷፮ የፖለቲካ ትምህርት ቤት እስከ ዛሬ ድረስ ለአብዮቱ ያበረከተውን አስተዋጽኦ እንደሚከተለው ማጠቃለል ይቻላል ።

ሀ- በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ካድሬዎችን አሠልጥኗል ።

ለ- በልዩ ልዩ ትምህርታዊ ስብሰባዎችና ሴሚናሮች ውይይት በማካሔድ በፕሮፓጋንዳና በቅስቀሳ ሥራ ተሳትፏል ።

ሐ- ትምህርታዊ ጽሑፎችን በማዘጋጀት ለሕዝባዊ ድርጅቶች ፤ ለውይይት ክበቦችና ለየጦር ግንባር አድሏል ።

መ- የማርክሲዝም-ሌኒንዝም መጻሕፍትንበውጭ ሀገርና በአማርኛ ቋንቋዎች የተጻፉትን እን ዳስፈላጊነቱ ለውይይት ክበቦች ፤ ለጦር ግንባሮች አድሏል ።

የየካቲት ፷፯ የፖለቲካ ት/ ቤት ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ለአብዮቱ ባደረገው ትግል ወቅት ከፀረ-አብዮተኞች በኩል ብዙ ሤራ ተሰንዝሮበታል ። በዚህም የትግል ዘመኑ ብዙ ካድሬ ዎቹ በፀረ-አብዮተኞች ሤራ የተነሳ ወድቀዋል ። ግምቱ ከፍ ያለ የት/ ቤቱ ንብረትም በፀረ-አብዮተ ኞች ወድሟል ። ለዚህ አንዱ ምሳሌ ከ80,000 በላይ መጻሕፍትና ንብረት በፀረ-ሕዝቦች ሊቃጠል የበቃ በት ሤራ ነው ።

የየካቲት ፷፯ የፖለቲካ ትምህርት ቤት እስ ከዛሬ ድረስ የሠራተኛው ከላይ የተጠቀሱት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ፤ በዚያው አቅጣጫ ወደፊት የሚ ሠራውን ለማጠናከርና አብዮቱ ዛሬ ለደረሰበት ከፍተኛ ደረጃ ከዚህ ትምህርት ቤት የሚጠይቀ ውን አስተዋጽኦ ለማሟላት መከናወን ያለባቸውን ተግባራት ከዚህ በታች ባጭር ባጭሩ በሚቀር ቡት ዓቢይ ነጥቦች ሊጠቃለሉ ይችላሉ ።





በፀረ-አብዮተኞች ከተቃጠለው የፖለቲካ ት/ቤት አንዱ ክፍል ። (በዚህ ቃጠሎ አያሌ የሶሻሊስት መጻሕፍትም ወድመዋል ።)

## ፩. በርዕዮተ ዓለም-ትምህርት ቤትነት ፡—

ሀ- በኅብረተሰቡ ውስጥ ማርክሲዝም ሌኒን ዝም ይበልጥ እንዲሠራጭ ለማድረግ የሚ ያስችሉ ለሰፊው ሕዝብ አብዮታዊ እንቅስ ቃሴ ትክክለኛ አመራር ሊሰጡ የሚችሉ ጥራት ያላቸው ካድሬዎችን በብዛት ማሠ ልጠን ፤

ለ- ማርክሳዊ ጽሑፎችን በማዘጋጀት ወይንም በመተርጐም (ቢቻል በልዩ ልዩ ብሔረሰብ ቋንቋዎች) በኅብረተሰብ ውስጥ እንዲሠ ራጭ ማድረግ ፤

ሐ- ማርክሳዊ በሆነ የአተናተን ዘዴ በፖለቲካ፤ በኤኮኖሚና በማኅበራዊ ኑሮ መስኮች የው ስጥና የውጭ ሁኔታዎችን በመገምገም የኢ ትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ የሚጠቅሙ ፤ የኢት ዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ከዓለም ጭቁን ሕዝቦች ጋር ትግሉን የሚያስተባብርበትን መንገድ የሚጠቁሙ ጥናቶችን ማዘጋጀት ፤

መ- ትምህርት ቤቱ የካድሬዎችን ብዛት ለመ ጨመር ከሚኖረው መሠረታዊ ዓላማ በመ ነሣት እስከዛሬ ድረስ ባገኛቸው የሥራ ልም ዶች በመመርኰዝ የተሟላ ድርጅትና ዝግ ጅት ያላቸው የፖለቲካ ትምህርት ቤቶች አማካይ በሆኑ ክፍለ ሀገሮች የሚፈቱበትን መንገድ ማጥናትና ማዘጋጀት ፤

## ፪. የፓርቲ ትምህርት ቤት ጥንስስ ፤

ዛሬ የወዝአደሩን ርዕዮተ ዓለም ለማስተዋወ ቅና ለማስፋፋት የተቋቋመው የፖለቲካ ትም ህርት ቤት ፤ ነገ የወዝአደሩ ፓርቲ ሲመሠ ረት ፓርቲው በልዩ ልዩ የሥራ መስኮችየሚ ከተላቸውን ፖሊሲዎች የሚያስፈጽሙ ካድ ሬዎች የሚሠለጥኑበት የፓርቲ ትምህርት ቤት ጥንስስ እንደመሆኑ መጠን ፤ ወደፊት የሚጠብቀው ኀላፊነት እስከ አሁን ከነበረው ይከብዳል ። ስለሆነም ይህንን ከባድ ኀላፊነት ለማቃለልና ባለውም ምቹ ሁኔታ በመጠቀም የወዝአደሩ ፓርቲ ከመፈጠሩም በፊት ሆነ ከአሁን ወዲያ በሚከተሉት አቅጣጫዎችላይ ማተኰር ያስፈልገዋል ። ላለንበት ታሪካዊ ወቅት የአብዮቱ የመገንባት ገጽ ከማፍረስ ገጹ የጐላ መሆን ስላለበት በፖለቲካ ትምህርት ቤት የሚሠለጥኑ ካድሬዎች የኢትዮጵያ አብ ዮት በፖለቲካ ፤ በኤኮኖሚ ፤ በማኅበራዊ ኑሮ ጉዳዮች ላይ ማከናወን በሚኖርበት ተግባሮች

እኳያ የሚረዱ መሆን ይኖርባቸዋል ። ስለዚ
ህም የየካቲት ፷፮ የፖለቲካ ትምህርት ቤት፡-

— የፖለቲካ ካድሬዎችን ፤

— የኤኮኖሚ ካድሬዎችን ፤

— የልዩ ልዩ ትምህርታዊና ማኅበራዊጉዳይ ካድሬዎችን በንቃትና ጥራት ባለውሁኔታ ለማሠልጠን አስፈላጊውን ማቴሪያላዊና የሰው ኃይል ዝግጅት አድርጎ የወደፊት ሥራውን በዚህ አቅጣጫ መቀየስ ግዴታቸው ይሆናል ። የሚያሠለጥናቸውም ካድሬዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባራት ለማከናወን የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል ።

ሀ- <u>ፖለቲካ ካድሬዎች ፤</u>

— ሕዝባዊ ድርጅቶች ፤ አብዮቱ ያስገኛቸውን ድሎች እንዲጠብቁና ለተጨማሪም ድሎች በተሻለ ዝግጅት እንዲታገሉ ለማድረግና በአጠቃላይም እንቅስቃሴአቸው አብዮቱን የሚጠቅምና የአብዮቱን ግስጋሴ በማያያዝ መልክ እንዲጠናከሩናሌሎችም ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ፤ ፀረ-ፊውዳልና ፀረ-ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት የብዙኃን ድርጅቶች ተፈጥረው ትክክለኛ የርዕዮተ ዓለም አመራር ለመስጠት የሚችሉ ፤



— ሰፊው ሕዝብ ወዳጅና ጠላቱን በሚገባ ለይቶ በማወቅ ገና ለሚጠብቀው ረጅምና መራራ ትግል እንዲዘጋጅ ንቃተ-ሕሊናውን ከፍ እንዲል የሚቀሰቅሱና የሚያነቁ

— አብዮቱ እስከዛሬ ድረስ ያላገኘውን ትክክለኛ አመራር ሊሰጥ የሚችለው የወዝ-አደሩ ፓርቲ ጠንካራ ማኅበራዊ መሠረት እንዲኖረው ከመፈጠሩ በፊትና ከተፈጠረም በኋላ የሚታገሉና የሚያታግሉ ፤

— በየጦር ግንባሩና በየጦር ሠፈሩ የመደበኛውን ሠራዊትና የሚሊሺያውን ንቃተ-ሕሊና ከፍ በማድረግ የተሰለፈበትን ዓላማ በትክክል እንዲረዳና ሞራሉም እንዲያድግ በቅስቀሳ ፤ በፕሮፓጋንዳና በማንቃት ሥራዎች የሚሠማሩ ፤



INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

ለ· <u>የኤኮኖሚ ካድሬዎች</u> ፡—

— ምርት እንዲያድግ፤ወዝአደሩን ወይንም ገበሬውን በግንባር ቀደምትነት የሚመሩና የሚያስተባብሩ ፤

— በኅብረት እርሻዎች ፤ በልዩ ልዩ የኅብረት ሥራ ማኅበሮችና የሥራ ዘርፎች የተሠማሩትን የኅብረተሰብ ክፍሎች በነኝሁ ድርጅቶች ውስጥ የሚያደርጉትን ተሳትፎ አስፈላጊነት በማስረዳት የሚያስተምሩና የሚቀሰቅሱ ፤

— ወዝአደሩ በየፋብሪካው አስተዳደር ውስጥ ጠቃሚ አስተዋጽኦ እንዲኖረው የሚያዘጋጁ ፤

— የማቴሪያልና የሰው ጉልበት አለምክንያት መባከን ጉጂነት በማስረዳት ሰፊው ሕዝብ ቁጠባን እንዲለምድ የሚቀሰቅሱ ፤

— ኅብረተሰቡ የምርት ኃይሎችን ለማሳደግ ሶሻሊስት ኤኮኖሚን ለመመሥረት በሚደረገው ትግል ግንባር ቀደም እንዲሆን ሕዝቡም በመፍጠር ችሎታ በመጠቀም



የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕውቀት እንዲቀስም በተግባርም እንዲያውለው በማድረግ ሰፊው ሕዝብ የአብዮቱ ማቴሪያላዊ ሁኔታ መሥራች መሆኑን የሚያምኑ የሚያረጋግጡ ፤

— ለሶሻሊዝም መሠረት የሚሆን ኤኮኖሚ እንዲጠነክር የሰፊው ሕዝብ ተሳትፎ ከፍ እንዲል ለማድረግ በግንባር ቀደምትነት የሚታገሉና የሚያታግሉ ፤

ሐ· <u>የልዩ ልዩ የሥራ መስኮች ካድሬዎች</u> ፡—

— የአስተዳደር ሥራ ፤ እንዲቀላጠፍ አመራር የሚሰጡ ፤

— የልዩ ልዩ መንግሥታዊ ተቋሞች በተቀነባበረ መልክና የአብዮቱን ግስጋሴ በሚያፋጥን ዓይነት መንገድ እንዲደራጅ አመራር የሚሰጡ ፤

— ሕዝቡ ራሱን በራሱ የማስተዳደር ልምድ እንዲጎለምስ የሚያስተምሩ ፤

— በባህል አቅጣጫ አድኃሪና ጎታች ባህሎች ተወግደው በምትካቸው ተራማጅ ባህሎችና ልምዶች እንዲዳብሩ የሚቀሰቅሱ፤



INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA

— የብሔረሰቦችን ራስን በራስ አገዛዝ (ሪጂናል አውቶኖሚ) መብት ተግባራዊ እንዲሆን ለማድረግ በዚህ አቅጣጫ የጭቁን ብሔረሰብ ጭቁን መደብ አባሎች ተሳትፎ እንዲሰፋና እንዲያድግ የሚያስተምሩ ፤



Proudly brought to you by

www.binyamhk.wordpress.com



INFINIX HOT 8 | 13MP
AI TRIPLE CAMERA